# ለእግዚአብሔር ፍቅር

"... እኔ የሚረባህን ነገር የማስተምርህ በምትሄድባትም መንገድ የምመራህ አምላክህ እግዚአብሔር ነኝ።" (ኢሳ 48 ÷ 17)

God's Love, P.O.Box 6734, Lee's Summit, MO, 64064. / E-mail – mtizazu@hotmail.com / Ph/Fax 816 – 246 – 9395

ሰኔ 1995 June 2003 "ልጆችሽም ሁሉ ከእግዚአብሔር የተማሩ ይሆናሉ ፤ የልጆችሽም ሰላም ብዙ ይሆናል።" (ኢሳ 54÷13)


# መስቀል



አንድ እስከ ሞት አፋፍ የተቸገረ ወጣት ነበረ። ችግሩንም ቢታገለውና÷ በልዩ ልዩ መንገድ ቢሞክረው ምንም መፍትሔ ማግኘት ስለተሳነው፦ በግምባሩ መሬት ላይ ወድቆ÷በታላቅ ለቅሶ፤ወደ እግዚአብሔር መፀለይ ጀመረ። "አቤቱ ጌታ ሆይ መስቀሌ እጅግ ከብዶኛል። ይህንን መስቀል ተሸክሜ ልከተልህ ፈጽሞ አቅቶኛልና አድነኝ። መቼም ያለ መስቀል አንተን መከተል አይቻልምና ሌላ ቀለል ያለ መስቀል ስጠኝ።" ሲል ፀለየ።

ጌታም ልጄ ሆይ፦ የተሸከምኸው መስቀል ከአቅምህ በላይ ከሆነብህ ፦ መልሰህ በዚህ የመስቀሎች መካዚን ውስጥ አስቀምጠው አለው። ወጣቱም በእፎይታ ጌታን ካመሰገነ በኋላ የከበደውን መስቀል ወስዶ ከመካዚኑ አሰቀመጠ። ከዚያም ጌታ ቀጠለና፦ በል አሁን ደግሞ ሂድና የሚመችህን መስቀል መርጠህ ውሰድ አለው። ወጣቱም፤መካዚኑን ከፍቶ ገባና በክፍሉ ውስጥ የተደረደሩትን ስፍር ቁጥር የሌላቸውን መስቀሎች ተመለከተ። ልዩ ልዩ መጠንና ክብደት ያላቸው ነበሩ። አንዳንዶቹ እጅግ ትላልቅ ስለ ነበሩ÷ "ይህን መሸከም የሚችል ሰው ይኖር ይሆን" በማለት ተደነቀ።



በክፍሉ ዙሪያ ከተመለከተ በኋላ በግድግዳው ተጠግቶ የቆመ አንድ አነስ ያለ መስቀል አገኘና በእፎይታ ተነፈሰ። ከዚያም "ጌታ ሆይ÷ያንን ከሁሉ የሚያንሰውን መስቀል አግኝቼአለሁ።" ሲል በቀስታ ተናገረ። ጌታም መለሰና፦ ልጄ ሆይ፦ እርሱማ አንተ ከበደኝ ብለህ የመለስኸው ነው፤ሲል መለሰለት። አቃተኝ ብሎ የመለሰው መስቀል÷ በመካዚን ከሞላው መስቀል ሁሉ ያነሰ ሆኖ ስለ ተገኘ ነው።

አንተስ? መስቀል ከብዶህ አስመርሮሃል? "ምን ነው ጌታ ከሁሉ የከበደውን መስቀል ያስሸከመኝ?" ባይ ነህ?

የጐረቤቶችህን ሕይወት ቀረብ ብለህ ብትመለከት ትጽናናለህ። መስቀልህ ምንድን ነው? ጤና ነው ? በየቤቱና በየሆስፒታሉ የሚገኙትን በሽተኞችና አካለ ስንኩሎችን ተመልከት። ትዳር ነው? ሩቅ ሳትሄድ ጐረቤትህን በቀስታ ስለ ትዳራቸው ጠይቅ። ችግር ነው? የሞቀ ቤት ውስጥ አድረው የማያውቁትን÷ትኩስ እንጀራ ከቀመሱ ብዙ ጊዜ የሆናቸውን÷ቤት አልባ ድሆችን ተመልከት። የወዳጅ ወይም የዘመድ ክህደት ነው? ኢየሱስን አስታውስ። ምናልባትም በአካባቢህ ከሚመላለሱት አንዱ የባሰ ክህደት ደርሶበት ይሆናል። አገልግሎት ነው? ወንሞችህ የሚያልፉበትን በቀስታ አስተውል። በዚህም ሁሉ አምላክህ እግዚአብሔር ማንንም የማይጥልና የማይረሳ አምልክ መሆኑን አትዘንጋ። ያለ ጥርጥር ጌታ ያለህበትን ሁኔታ ያውቃል። የሚያሳዝንህ ያሳዝነዋል። በሚከፋህም ይከፋዋል። ምክንያቱም እግዚአብሔር ይወድሃል።

"ወዳጆች ሆይ÷በእናንተ መካከል እንደ እሳት ሊፈትናችሁ ስለሚሆነው መከራ ድንቅ ነገር እንደ መጣባችሁ አትደነቁ፤ ነገር ግን ክብሩ ሲገለጥ ደግሞ ሐሤት እያደረጋችሁ ደስ እንዲላችሁ÷ በክርስቶስ መከራ በምትካፈሉበት ልክ ደስ ይበላችሁ።" (1ጴጥሮስ 4÷12-13)

"በክርስቶስ ኢየሱስ ወደ ዘላለም ክብሩ የጠራችሁ የጸጋ ሁሉ አምላክ ለጥቂት ጊዜ መከራን ከተቀበላችሁ በኋላ÷ ራሱ ፍጹማን ያደርጋችኋል፡ ያጸናችሁማል፡ ያበረታችሁማል። ለእርሱ ክብርና ኃይል እስከ ዘላለም ድረስ ይሁን፤አሜን።" (1ጴጥሮስ 5÷10-11)

" ... <u>በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ፤ ነገር ግን አይዞአችሁ፤ እኔ ዓለምን አሸንፌዋለሁ</u>።" (የዮሐንስ ወንጌል 16÷33)

"... እኔ ከአንተ ጋር ነኝና አትፍራ፤እኔ አምላክህ ነኝና አትደንግጥ፤ አበረታሃለሁ÷እረዳህማለሁ÷በጽድቄም ቀኝ ደግፌ እይዝሃለሁ።" (ትንቢተ ኢሳይያስ 41÷10)

መስቀል የሚወደድ ነገር አይደለም። ነገር ግን የእግዚአብሔር ፈቃድ ሊሆን ይችላል ። መስቀልህ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የተቀበልኸው ከሆነ መሸከሙን የሚያስችል በቂ ጸጋ እንደ መና በየቀኑ ከሰማይ ይመጣል። ጸጋው ሁል ጊዜ በቂ ነው። መከራ ቢበዛ ጸጋውም እንዲሁ ይበዛል። የእግዚአብሔር ቸርነትና ታማኝነት ይህንን ያደርጋል። ጌታንና መስቀሉን አስብ። ብትወድቅም ርዳታ ይመጣልና አይዞህ ። አይዞሽ ።



# የተጨነቁትን መርዳት

ወዳጅህ ወይም ዘመድህ ወይም የምታውቀው ሰው÷ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ÷ ጠባዩ ተለውጦብሃል? ተስፋ መቁረጥ የሚያዘወትር ሰው ታውቃለህ ? ስለ ዚህ ሰው ሃሳብና ስጋት ይሰማሃል?

መልካም ስግተሃል። (SPAN) በሚባለው (ራስን የመግደል ማስወገጃ ብሔራዊ ድርጅት) መሠረት÷ይህ የዲፕሬሽን ምልክት ነው። ይህም በአማርኛ (ከልክ ያለፈ ጭንቀት) ሊባል ይችላል። የአእምሮ ሕመም ዓይነት የሆነው ይህ በሽታ ሰዎች ራሳቸውን ለመግደል እንዲያስቡ የማድረግ ጠባይ አለው

ብዙዎች እንደሚያስቡት ራሳቸውን የሚገድሉ ሰዎች ቁጥር ጥቂት አይደለም። NIMH ብሔራው የአእምሮ ጤንነት ማሰልጠኛ ባወጣው ዘገባ መሠረት÷ በ1997 ዓም በአሜሪካን ሐገር 8 ተኛው የነፍስ መጥፋት ምክንያት ራስን መግደል ነበረ። የአሜሪካን መንግሥት ይህንን ምክንያት በማድረግ÷ ነው በ1999 ዓም ልዩ ርምጃ መውሰድ የጀመረው።

የራስን ሕይወት ለማጥፋት በቂ የሆነ ምክያት ለማንም ሊኖር አይችልም የሰው ችግር የቱንም ያክል ቢከፋ በሕይወቱ ላይ ጥፋትን ማድረሱ የከፋ ነው። ይሁን እንጂ ለዚህ የሚያደርሰው ይህ ዲፕሬሽን የተባለው በሽታ መድኃኒት ያለው ሆኖም ውስብስብ ጠባይ አለው። ለምሳሌ ራሳቸውን ከሚገድሉ መቶ ሰዎች መሐከል ዘጠናዎቹ ዲፕሬሽን ወይም ተመሳሳይ የአእምሮ በሽታ እንዳለባቸው ታውቆአል።

በአሁኑ ጊዜ ብዙ ምርምሮች ውጤት ማስገኘት ስለ ጀመሩ÷ ራስን ለማጥፋት ስሜት÷ በሰው አእምሮ ውስጥ የሚገኝ <u>ሴራቶኒን</u> የሚባል ንጥረ ነገር ተጠያቂ መሆኑ ተደርሶበታል።ዲፕሬሽን ያለባቸው ሰዎች ሲመረመሩ በአእምሮአቸው ውስጥ ይህ ንጥረ ነገር አነስተኛ ሆኖ ተገኝቷል።

ራሳቸውን ለማጥፋት ሃሳብ ያላቸው ሰዎች÷"ሰው ምን ይለኛል"ማለት ስለሚያበዙ አብዛኛውን ጊዜ ሕክምና አይሄዱም። እንግዲህ የወዳጅ÷የዘመድ ወይም የጓደኛ ጥቅም እዚህ ላይ ነው። የመተዛዘንና የመተያየት አስፈላጊነት እዚህ ላይ ነው። ልብ አድርጎ መተያየትና በመተሳሰብ አብሮ መኖር ጥቅሙ እዚህ ላይ ነው።

# ጥቂት ምልክቶች

የሰው ችግርን የመቋቋም ችሎታው ስለሚለያይ÷ ራሱን ለመጉዳት የሚያስብን ሰው፦ በትክክል መረዳት ያዳግታል። ነገር ግን የሚከተሉት ሁኔታዎችና ምልክቶች÷ራሰን ለመጉዳት ከማሰብ ጋር እጅግ የሚገናኙ ናቸው።

⦿ በዘመድ ሞት÷በፍቺ ወይም በአደገኛ በሽታ ውስጥ የሚያልፉ ሰዎች

- ⦿ ዲፕሬሽን ያለባቸውና ዕጽ የሚጠቀሙ ሰዎች፡-
- ⦿ አለ ወትሮ ተስፋ መቁረጥን፥ ጉልበት ማጣትን ፥ ራስን መጣልና ሐዘንን የሚያበዙ ፡-
- ⦿ በሥራቸው ወይም በትምሕርታቸው ያለ ወትሮአቸው መጥፎ ውጤትና ፍላጎት የሚያሳዩ፡-
- ⦿ ከወዳጅ ዘመድና ከማሕበራዊ ኑሮ ራሳቸውን የሚያገልሉ፡-
- ⦿ የምግብ ፍላጎትና እንቅልፍ የጠፋባቸው፡-
- ⦿ ስለሞትና ራስን ስለ መግደል የሚናገሩ፡-
- ⦿ ንብረታቸውን አለወትሮ ለሰው በመስጠት የሚሰናበቱ ወዘተ፡-

## እንዴት መርዳት እንደሚቻል

በ SPAN መሠረት በአሜሪካን ሐገር በየ 42ቱ ሰኮንድ አንድ ራስን የመግደል ሙከራ ይደረጋል። በየ 17ቱ ደቂቃ ደግሞ አንድ ሰው ነፍሱን ያጠፋል። ሆኖም ይህ ሁኔታ በመድኃኒት ርዳታ የሚወገድ የጤና ጉዳይ እንጂ በሌላ መልክ ሊታይ አይገባም።

ስለዚህ ሰው ራሱን ስለመግደል ሲናገር ከሰማህ ልብ አድርገህ አስተውል። እንደ ቀላልም አትውሰድ።

ጥያቄ በመጠየቅ፡ ሳትፈራ የግለሰቡን ሁኔታ ለመረዳት ሞክር። ሞትን መፈለግ የጤና ምልክት ስላልሆነ የሐኪም እርዳታ እንዲያገኝ ግድ በለው።

እንዲህ ያለ ሰው ራሱን መግደል መፈለጉን በሚስጢር ለመያዝ ቢፈልግ መተባበር አይገባም። ሞት በሚስጢር የሚያዝበት ምክንያት የለምና። ከሰውየው መብት ይልቅ ደኅንነቱ መቅደም አለበት።

ራሳቸውን ከገደሉት መቶ ሰዎች መሐከል ስድሳዎቹ በጠብመንጃ የተጠቀሙ መሆኑ በጥናት ስለ ተረጋገጠ፡- ለጥንቃቄ ያህል፥ ምንም ዓይነት ጠብ መንጃ በቤቱ ቢኖር ፈጥነህ አስወግድ።
(Matters of Concern) ከሚል የጤና ጥበቃ መልዕክት የተተረጎመ)

በመጨረሻም፡- ይህ በእኔ አካባቢ ሊደርስ አይችልም ብለህ አታስብ። የዚህ ደብዳቤ አዘጋጅ በምኖርበት ከተማ እአአ ከ1990 እስከ 1998 ገደማ ብቻ ሦስት የምናውቃቸው የሐገራችን ሰዎች ራሳቸውን አጥፍተዋል። ሰዎች ደኅና መስለው ስለሚንቀሳቀሱ ብቻ ቸል ልንላቸው አይገባም ለማለት ነው። አንዳንዴ በመልካም የፍቅር ማጽናናት ብቻ ሰውን ከዚህ ክፉ ርምጃ መመለስ ይቻላል። የተጨነቁትን በፍቅር እንደ መርዳት እግዚአብሔርን የሚያስደስተው ምን አለ?

# ምስክርነት

........................ካለፈው የቀጠለ

*<u>ደኅንነት የእግዚአብሔር ሥራ ነው።</u>*

*በዮሐንስ ወንጌል 6፥44 "የላከኝ አብ ከሳበው በቀር ወደ እኔ ሊመጣ የሚችል የለም፥ ..." ተብሎ እንደ ተጻፈው፡-* መንፈስ ቅዱስ የሰውን ልብ ካልነካ በቀር በሰው ጥረት ብቻ ወደ ጌታ ዕውቀት መድረስ ፈጽሞ አይቻልም። ሁላችንን ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት ያስቻለን፡- በመንፈስ ቅዱስ የሚሠራ የጌታ ጸጋ ነው። ይህንኑ አስመልክቶ ሐዋሪያው ጳውሎስ የቆሮንቶስ ሰዎችን ሲያስተምር እንደ ጻፈው፡- "እኔ ተከልሁ አጵሎስም አጠጣ፡ ነገር ግን እግዚአብሔር ያሳድግ ነበር ፤ እንግዲያስ የሚያሳድግ እግዚአብሔር እንጂ የሚተክል ቢሆን ወይም የሚያጠጣ ቢሆን አንዳች አይደለም። የሚተክልና የሚያጠጣ አንድ ናቸው ፥ ነገር ግን እያንዳንዱ እንደ ራሱ ድካም መጠን የራሱን ደመወዝ ይቀበላል።" ይላል።
(1ቆሮ 3 ፥ 7 - 8)

የሰዎችን ልብ ለመለወጥ እኔና እናንተ ምንም ችሎታ የለንም። አንድ ቢሊ ግራም ሲናገሩ የሰማሁትን ታሪክ ልንገራችሁ አንድ ቀን ቢሊ ግራም በአይሮፕላን ወደ አንድ ቦታ ሲበሩ ከተሳፋሪዎቹ አንዱ እጅግ የሰከረ ነበረ። እርሱም ወንጌላዊው ቢሊ ግራም በአይሮፕላኑ ውስጥ መኖራቸውን በሰማ ጊዜ እንዲያገናኙት አስተናጋጆቹን ግድ አላቸው። አስተናጋጆቹም ዝም ሊያሰኙት መቸገራቸውን በተረዱ ጊዜ ቢሊ ተነሥተው ሰካሩ ሰው ወደ ተቀመጠበት ሄደው ሰላምታ አቀረቡለት። በዚህን ጊዜ ሰካሩ ሰው "ሰላም ቢሊ፥ ስለ ተገናኘን ደስ ብሎኛል። እኔ በአንተ ከተለወጡት ሰዎች አንዱ ነኝ" (I am one of your converts) አላቸው። በዚህ ጊዜ ቢሊ በልባቸው፡- ምናልባት በእኔ ተለውጠህ ይሆናል። በእርግጥ ጌታ ግን አልለወጠህም አሉት።

በሰው ሕይወት እውነተኛ ለውጥ ማድረግ የእግዚአብሔር ብቻ ችሎታ ነው። በወንጌላችን አቀራረብ፡አንዳንድ ጊዜ ውጤት ለማግኘት ግፊት ማድረግ ይሰማናል። ጊዜው ሆነ አልሆነ፥በራሳችን ስሜት ሰዎች ውሳኔ እንዲያደርጉ እንቸኩላለን። ነገር ግን ድርሻችንን በትክክል ብንረዳ፥ የእኛ ፈንታ፡- ወንጌልን በመጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥራትና በግልጽ ለሰዎች በማቅረብ ውጤቱን ለእግዚአብሔር መተው ነው። የመሰከርንላቸው ሰዎች ልባቸውን ለጌታ ከከፈቱ በፀሎት ልንመራቸው መዘጋጀት አግባብ ነው። ሆኖም ምስክርነታችን ወዲያው ውጤት ባያሳይ በእግዚአብሔር እጅ መተውን ማወቅ ያስፈልጋል።

## *እግዚአብሔር ሰዎችን ወደ ራሱ ለመምራት ሊጠቀምብህ ይችላል*

በእስታትስቲክ እንደ ተረጋገጠው ከአማኞች መሐከል ዘጠና አምስት ከመቶ እጁ አንድም ሰው ወደ ጌታ መርተው አያውቁም። አንተ ከየትኛው ወገን ነህ? በአንተ ድፍረትና ትጋት ምክንያት ከጨለማ ወደ ብርሃን የተሸጋገረ ሰው አለ?

ምንም እንኳን በተለይ ለወንጌላዊነት የሚጠሩ ሰዎች ቢኖሩም፥ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሰዎችን መጋበዝና መምራት የጥቂት ሰዎች ሥራ ስላይደለ፥ ከወደድህና ከታዘዝህ፥ ጌታ በእርግጥ ይጠቀምብሃል። ሰውን ወደ ጌታ ለመምራት ልዩ ስጦታና ችሎታ ያላቸውን ወንጌላውያን ተመልክተህ በራስህ ተስፋ መቁረጥ የለብህም። ምክንያቱም አንድም የመጽሐፍ ቅዱስን እውነት ማጥናት ብቁ ያደርግሃል፤ እንዲሁም የወንጌልን እውነት በተጨባጭ ለሰው የማቅረብ ትክክለኛ መንገድን መማር ትችላለህ። ወንጌል ወንጌልነቱን እንዳያጣ መጠንቀቅ እንዴት እንደሚገባ መማር ይቻላል። ... ይቀጥላል

❖ ❖ ❖ ❖ ❖ ❖ ❖

# ምስጋና

በዚህ አገልግሎታችን በፀሎት፡ በምክርና በገንዘብ አስተዋጽዖ አብራችሁን የቆማችሁ ወገኖቻችን ሁሉ፥ጌታ እንደ ባለጸጋነቱ አብዝቶ ይባርካችሁ። በተለይም ወንድም ሐብታሙ ከለቻና እህታችን ገነት ያረጋል ከካንሳስ፥ ጌታ ቸርነታችሁን ያስብላችሁ።

ወንድም ሰሙ መታፈሪያ ከሙዙሪ፡- መልክታችንን ለማባዛት የሚያስፈልገውን ወጪ በመሸፈን ከአገልግሎታችን ጋር ለመቆም በመፍቀድህ የአገልግሎቱ ባለቤት ጌታ ኢየሱስ ከክብሩ ያስብልህ። በጣም እናመሰግናለን።

❖ ❖ ❖ ❖ ❖ ❖ ❖

በአሁኑ ጊዜ መልክታችን በአብዛኛው የሚሰራጨው በሰሜን አሜሪካን ቢሆንም፥ በዓለም አቀፍ እየሰፋን ነው። በኢትዮጵያ፥ ጅቡቲ፥ ኬኒያ፥ ሊባኖስ፥ ጀርመን፥ ስዊድን፥ በኢጣሊያና በአውስትራሊያ መጠነኛ ስርጭት አለን።

መልዕክታችን የሚባርካችሁ ከሆነ ለወገኖች አስተዋውቁን። አድራሻዎች ሰብስባችሁ በደብዳቤ ወይም በኢ- ደብዳቤ ወይም በፋክስ ላኩልን፡

**አድራሻችን በድጋሚ፡-**

God's Love
P.O.Box 6734
Lee's Summit MO 64064
USA

Fax 816-246-9395

E-mail mtizazu@hotmail.com
የዌብ መድረክ እየተሠራ ነው።

አስተያየታችሁን ጻፉልን። የሚያበረታታና የሚያሳድግ ምክርና አስተያየት ብትሰጡን በጌታ ሥራ ታሳድጉናላችሁ። ጌታ ይባርካችሁ።

## → <u>ደኅንነት</u> ←

"እውነት እውነት እልሃለሁ፥ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር <u>የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ</u> አይችልም" (የዮሐንስ ወንጌል 3፥3)

"ኢየሱስ ጌታ እንደ ሆነ በአፍህ ብትመሰክር እግዚአብሔርም ከሙታን እንዳስነሣው በልብህ ብታምን <u>ትድናለህና</u>፤ ሰው በልቡ አምኖ ይጸድቃልና፡ በአፉም መስክሮ <u>ይድናልና</u>። (ሮሜ 10፥ 9-10)

"ያመነ የተጠመቀም <u>ይድናል</u>፥ያላመነ ግን ይፈረድበታል። (የማርቆስ ወንጌል 16 ፥ 16)